# የ 2022 /2015 ዓ.ም የዓለም ኤድስ ቀን

በከተማ አስተዳደር/ በክ/ከተማ በወረዳ እና ፈፃሚ አካላት (ሴክተሮች)

የሚተገበር የመነሻ ሰነድ

**Equalize**

**“Putting Ourselves to the Test:**

**Achieving Equity to End HIV”**

ፍትሀዊና ተደራሽ የኤች አይ ቪ/ኤድስ አገልግሎት!!

መግቢያ

ኤች አይ ቪ መከሰቱ ከታወቀበት እ.ኤ.አ ከ1981 ጀምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ32.7 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ሕይወታቸውን በኤድስ ምክንያት ያጡ ሲሆን 38 ሚሊዮን ሰዎች ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ኤችአይቪ በደማቸው እንደሚገኝ ይገመታል። በየዓመቱ 1.7 ሚሊዮን የሚሆኑ አዲስ በኤችአይቪ የሚያዙ ሰዎች እንዳሉና 690,000 ሰዎች ለህልፈት እንደሚዳረጉ መረጃዎች ያሳያሉ።

የሀገራችን የኤች አይ ቪ የስርጭት ምጣኔ 0.93% ሲሆን በዚህም ስሌት 617,000 የሚሆኑ ወገኖች ኤችአይቪ በደማቸው እንደሚገኝ ከእነዚህም ውስጥ 61% ያህሉ ሴቶች መሆናውን ጥናቶች ያሳያሉ። ሆኖም የስርጭቱ ምጣኔ ከክልል ክልል፣ ከአንድ ቦታ ሌላ ቦታ፣ በተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች እንዲሁም በከተማና በገጠር በከፍተኛ ደረጃ የሚለያይና አዳዲስ በኤችአይቪ የመያዝ ምጣኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚፈለገው መጠን እየቀነሰ እንዳልሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ።

ይበልጥ ተጋላጭ የማበረሰብ ክፍሎች የስርጭት ምጣኔ ከአጠቃላይ ማህበረሰቡ የስርጭት ምጣኔ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ በቅርብ የተጠናው ጥናት የሴተኛ አዳሪዎች (18 %) በላይ መሆኑን ያሳያል ። የአፍላዎችና ወጣቶች ለኤችአይቪ ያላቸው ተጋላጭነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱና የችግሩ ስፋት ከፍተኛ እንደሆነ ሌላው ማሳያ ነው። ከዚህም በተጨማሪ አዲስ በኤችአይቪ የመያዝ ምጣኔን ለመቀነስ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ኤችአይቪ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍን መከላከል ሲሆን አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ የተፈለገውን ውጤት ማምጣት አለመቻሉን ያሳያል። በመሆኑም የተሻለ ውጤት ለማጣት ከፍተኛ ጥረትን የሚጠይቅ ነው።

አዲስ በኤችአይቪ የሚያዙ ሰዎችን መከላከል የሚቻልበት ሌላው ዋነኛ ስልት የኮንዶም ፕሮግራምን ተግባራዊ በማደረግ አቅርቦቱን በአስተማማኝ ደረጃ ማጠናከር ቢሆንም በአገር ደረጃ የኮንዶም አቅርቦት በበቂ ሁኔታ አለመኖር የመከላከሉን ስራ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል።

ስለሆነም በዘንድሮው የዓለም ኤድስ ቀን ተጨባጭ ውጤት ሊያመጣ የሚችል ንቅናቄ በየደረጃው በመፍጠር ሁሉም አካል በባለቤትነት፤ በተጠያቂነት እና በኃላፊነት ስሜት ምላሽ እንዲሰጥ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች መተላለፍ ይኖርባቸዋል።

በዚህም መሰረት የዘንድሮው የዓለም ኤድስ ቀን በእንግሊዘኛ "EQUALIZE" በአማርኛ "ፍትሀዊና ተደራሽ የኤችአይቪ/ኤድስ አገልግሎት" በሚል መሪ ቃል ህዳር 22 ቀን 2015 ዓ.ም በደመቀ ሁኔታ ይከበራል።

ዘንድሮው የዓለም ኤድስ ቀን እንደ ወትሮው ሁሉ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ኤችአይቪ በደማቸው ለሚገኝባቸውና በኤችአይቪ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ድጋፋቸውን ለማሳየት፤ በኤድስ ህይወታቸውን ያጡትን ወገኖች ለማስታወስ እና ወረርሽኙን ለመቆጣጠር ይበልጥ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን ማዕከል ያደረገ የባህሪ ለውጥ ስራ በመስራት ወደ ምርመራና የህክምና አገልግሎት እንዲገቡ ለማድረግ ህዳር 22 ቀን የሚከበረውን የዓለም ኤድስ ቀን እንደ አንድ ዋና የንቅናቄ መፍጠሪያ መድረክ በማድረግ መጠቀም ይገባናል።

በተለይም የዚህ ዓመት የዓለም ኤድስ ቀን መነሻ ሃሳቡ ያደረገው አገልግሎቶችን በእኩልነት፤ በፍትሃዊነት እና በተደራሽነት ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነው።

የአመራሩና የማህበረሠቡ ተሳትፎ ለኤችአይቪ/ኤድስ ዘርፈ-ብዙ ምላሽ ስኬት የማይተካ ሚና እንደነበረው የሚዘነጋ ባይሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ አመራሩ ለኤችአይቪ የሚሰጠው ትኩረት እያጣ መምጣቱ ወረርሽኙን በአጭር ጊዜ ለመቆቆጣጠር አልተቻለም። በሌላ በኩል ይበልጥ ተጋላጭ የማበረሰብ ክፍሎችን ለይቶ እና ተጋላጭ ተኮር የመከላከል ስራ በመስራት በኩል በሁሉም ባለቤቶችና ፈፃሚዎች ዘንድ ከፍተኛ መዘናጋት ይታያል። የባሪ ለውጥ ስራውን ከምርመራው ጋር አስተሳስሮ በመሄድ በኩልም ከፍተኛ  የሆነ ክፍተት አለ። ለኤችአይቪ ከፍተኛ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍል የያዙ ሴክተር አመራሮችም ለኤችአይቪ መከላከል እየሰጡት ያለው ምላሽ በእጅጉ የቀነሰ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የኤችአይቪ መከላልና መቆጣጠር ስራዎችን እንዲሰሩ ተቋቁመው የነበሩ የስራ መደቦች እየፈረሱና እየታጠፉ መሆናቸው እንዲሁም ያሉትም ደግሞ የሰው ሃይላቸው ከቦታው እየተነሱ ባለቤት አጥቷል። እነዚህ ሴክተሮች የያዙት የሰው ሓይል ለኤችአይቪ ይበልጥ ተጋላጭ ግን ደግሞ አምራች ኃይል ሲሆን ከስራው ወይም ከልማቱ ጎን ለጎን ራሱንና ቤተሰቡን ከኤችአይቪ መከላከል እዲችል ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረለትም።

በማበረሰብ ደረጃም ውጤት የመጣበት የማበረሰብ ባለቤትነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ በመምጣቱ የማህበረሰቡ ንቁ ተሳትፎና ለጋራ ዓላማ በትብብር በኤችአይቪ/ኤድስ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች መረጃ፣ አገልግሎት፣ ማህበራዊ ጥበቃዎች ተጠናክረው መቀጠል ሲገባቸው በእጅጉ ተቀዛቅዟል። ለጋሽ ድርጅቶች፣ የኃይማኖት መሪዎች፣ ሲቪክ ማህበራትና እያንዳንዱ ግለሰብ የተሻለ የኤችአይቪ ስርጭት በመግታት ጤናማና ለመኖር ምቹ የሆነች ሀገር በመገንባት ሂደቱ የቀደመ የማይተካ አሻራቸውን ማሳረፍ ይጠበቅባቸዋል። የዚህ ዓመት የዓለም ኤድስ ቀንም ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ክፍተቶችን በማረምና መልካም ጎኖችን አጠናክሮ ማስቀጠል።

የፖለቲካ መሪዎችን ቁርጠኝነት በየጊዜው ማግኘት በማበረሰቡና በፈጻሚው አካል በኩል በጎ ተፅዕኖ ሊፈጥር እንደሚችል እና ተፈላጊ ለውጦችንም በተፈለገው ልክ ማድረስ እንደሚቻል ከአስር ዓመት በፊት ያስመዘገብነው በኤችአይቪ አዲስ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር እና የሞት ምጣኔ በእጅጉ መቀነስ ምስክር ነው። የአመራሩን ሚና በኮቪድ-19 ወረርሽኝም የታየ ነው።  ዛሬም ኤችአይቪ/ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር የአመራሩን ትኩረት ይሻል። እ.ኤ.አ በ 2030 ኤድስ የማህበረሰቡ የጤና ችግር የማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ በተያዘው ዕቅድ የመጨረሻዎቹ አስር ዓመታት ላይ እንደመገኘታችን መጠን ከግቡ ለመድረስ ከዚህ በፊት ውጤት ያስመዘገብንበትን የአመራር ቁርጠኝነት መልሰን ማረጋገጥ ተተኪ የሌለው መፍትሄ ነው።

በሀገራችን የኤች አይ ቪ/ኤድስ ዘርፈ-ብዙ ምላሽ የተመዘገቡ ውጤቶች  በዘላቂነት አስጠብቆ በማስኬድ በኩል እያጋጠሙ ያሉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች፡-

በ 2015 የዓለም ኤድስ ቀንን እንደመልካም አጋጣሚ በመቁጠር የተመዘገቡ ውጤቶች ወደ ኋዋላ እንዳይመለሱ እና እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች ከዚህ ቀጥሎ የተመላከቱ ሲሆን የተመዘገበው ውጤት በየደረጃው ያለው አመራር አጀንዳው እንዲያደርገው ከጤና ሚ/ር ጀምሮ እስከ ወረዳ ያለው የጤና መዋቅር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግና በተለያዩ ፕሮግራሞች አመራሩ የተገኘበት የምክክርና የንቅናቄ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡

<u>ተግዳሮቶች</u>

አሁን ላይ ያጋጠመውን መዘናጋት እና ተገቢ ያልሆነ ቸልተኝነት መቀልበስ ካልተቻለ ምናልባትም እንደ አንዳንድ የአፍሪካ አገሮች የስርጭቱ ሁኔታ የአገር ስጋት የማይሆንበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ አሁን ከተፈጠረው መዘናጋት መውጣት እና የተገኘውን ውጤት በማስቀጠል በ 2030 ኤድስ የማህበረሰቡ የጤና ችግር ወደ ማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ መስራት ያስፈልጋል፡፡

- ለኤችአይቪ/ኤድስ መከላልና መቆጣጠር ተብሎ የተቋቋሙ መዋቅሮች መፍረስ፡- እጅግ በርካታ ሴክተሮች የሰው ኃይልና መዋቅሩን ማፍረሳቸው በየሴክተሩ ይደረግ የነበረው የመከላከል ስራ እንደፈርስ መደረጉ፡፡ ለምሳሌ የትምህርት ሴክተሩን እና ሴቶች እና ማህበርዊ ሴክተሮች ብንወስድ አብላጫውን የማህበረሰብ ክፍል የያዘው እና ለኤችአይቪ በከፍተኛ ሁኔታ ሊጋለጥ የሚችለውን ወጣት በየያዘው ሴክተር መዋቅሩን አጠናክሮ መሄድ ሲገባው አንድና ሁለት ሰው ብቻ በመመደብ ለዚያውም በጎ ተፅዕኖ እንዲያመጣ በሚቸል መንገድ አለመዋቀሩ፡፡
- የአመራር ትኩረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠፋ መምጣት፡- ከዚህ ቀደም ብሎ ለተመዘገበው የዘርፈ-ብዙ ምላሹ ስኬት ከፍተኛ ሚና የነበረው የአመራሩ ቁርጠኝነት ዛሬ ላይ መታየት አለመቻል ዋናነኛው ተግዳሮት ሲሆን ማሳያዎቹም የአመራር አደረጃጀቶች (ኤድስ ምክር ቤት ፣ የሥራ አመራር ቦርድ በሚፈለገው መልኩ አለመቋቋምና አለመጠናከር)፣ ተቋማት የኤችአይቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ ፕሮግራሞችን በባለቤትነት አለመተግበር ከችግሩ አስቸኳይነትና አሳሳቢነት አንፃር ጉዳዩ የሚፈልገውን የሰውና የገንዘብ ኃይል በወቅቱ የማግኘት ተግዳሮት በዘርፈ-ብዙ ምላሹ ላይ እያጋጠሙ ካሉት ተግዳሮቶች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
- ተጋላጭ ተኮር የመከላከል ስራው እየተቀዛቀዘ መምጣት፣ ይበልጥ ተጋላጭና ትኩረት የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎችን ወደ ምርመራ እንዲመጡ የሚያግዝ የባህሪ ለውጥ ስራዎች በስፋትና በተደራሽነት እየተተገበሩ አለመሆኑ የሶስት 95 ግቦችን በተለይም የመጀመሪያውን ዘጠና ማሳካት አልተቻለም፡፡ ይህ ደግሞ ወረርሽኙን ለመቆጣር የሚደረገውን ጉዞ በእጅጉ እየጠፈታተነው ይገኛል፡፡
- ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ የማበረሰብ ክፍሎች ማህበራት መፍረስ፡- ማህበራት ከተቋቋሙባቸው ዓላማ አንጻር በመጀመሪያዎቹ ዓማታት ፋና ወጊ ሁነው እና ዋጋ ከፍለው ትውልድ ይዳን በእኛ ይብቃ ብለው ወገናቸውን ታድገዋል፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ ማህበራት ዛሬ ላይ በርካቶቹ ድጋፍ በማጣታቸው ፈርሰዋል፡፡
- ኤችአይቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለማድረግ የተያዘውን ግብ ለማሳካት በሁሉም ባለድርሻ አካላት ተከታታይነት ያላቸዉ ፕሮግራሞች ቢተገበሩም በማህበረሰብ ደረጃ የሚተገበሩ ስራዎች መቀዛቀዝ ዛሬም አፈጻጸሙ ወደ ሚፈለገው ደረጃ አልደረሰም፡፡

**የ 2015 ዓም ዓለም ኤድስ ቀን በየደረጃው ሲከበር ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች፡-**

የኤችአይቪ/ኤድስ ዘርፈ-ብዙ ምላሽን ጨምሮ ዓለማቀፋዊ የጤና ምላሽ አሰጣጥን እንደሀገር የተገኙ ስኬቶችን በማጠናከር ያጋጠሙንን ተግዳሮቶች አዳዲስ አሰራሮችን በመዘርጋት በአዲስ መልክ መቃኘት ይኖርብናል። በመሆኑም እንደሀገር ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነትን በመጋራት በትብብር በመስራት ቀጥሎ የተጠቀሱትን ዋና ዋና ነጥቦች ማረጋገጥ ይቻላል።

- በመንግስት ሴክተሮች ያሉ መዋቅሮች ለኤችአይቪ መከላከል ስራ ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ።
- ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኙ ወገኖችን በድጋፍና ክብካቤ ማገዝ ማህበራትም እንዲጠናከሩ መስራት።
- ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የማበረሰብ ክፍሎች ትኩረት መስጠት
- አድሎና መገለልን ሊያስገድ የሚችል ስራዎ ችን መዘስራት
- የኤችአይቪ/ኤድስ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ማረጋገጥ፡- የፀረ-ኤችአይቪ መድሃኒት፣ የኤችአይቪ ምርመራ እና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው የጤና አገልግሎቶችን ለሁሉም ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮችና የማህበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ ማድረግ ይጠበቅብናል።
- የኤችአይቪ ፕሮግራሞች የሴቶችና የልጃገረዶችን መብትና የፆታ እኩልነት ያማከሉ እንዲሆኑ ማድረግ፡- ኤችአይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ሴቶች እና ልጃገረዶች ተሳትፎ እና ውሳኔ የመስጠት ሚና ሊኖራቸው ይገባል። በየደረጃው የሚቀረፁ የኤችአይቪ ፕሮግራሞች አሳታፊና ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው።

**በ 2015 ዓ.ም የዓለም ኤድስ ቀን አከባበርን በተመለከተ ሴክተር መ/ቤቶች፣ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ ዝግጅቶች**

**1. ከበዓሉ በፊት የሚከናወኑ (Pre-WAD 2022 Activities) ተግባራት፡-**

የ 2022 መሪ ቃል በእንግሊዘኛ “Equality” በአማርኛ “ፍትሀዊና ተደራሽ የኤችአይቪ/ኤድስ አገልግሎት” በሚል ሲሆን በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ፀረ-ኤችአይቪ አገልግሎቶችን ተደራሽ ለማድረግ የተጠናከረ የመከላከልና የመቆጣጠር ምላሽ እንዲኖር ለማድረግ የታሰበ ስለሆነ በሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲታወቅና እንዲተገበር ማድረግ

- በዓሉን በደመቀ ሁኔታ ሊያስተባብር እና ሊመራ የሚችል ግብረኃይል ማቋቋም። የግበረሄሉ ስብጥርም የመንግስት ሴክተሮችን የሚወክል፤ አጋር ድርጅቶችን ፤ሲቪክ ማህበራትን እና የማህበረሰብ ውክልና ያላቸውን ሰዎች ያካተተ ሊሆን ይገባል።
- የዕለቱን መሪ ቃል እና ዋና ጭብጡን መሰረት በማድረግ በተለያዩ ኩነቶች ማለትም የቅስቀሳና የሞቢላይዜሽን ሥራዎችን በማከናወን የሚዲያ ሽፋን እንዲኖር ማድረግና የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተላለፍ።

- ከበዓሉ ቀን በፊት በሚኖሩ ቀናቶች  የአደባባይ ትዕይንቶችን (የጎዳና ላይ የሠርከስ ትርኢት) ማሳየት እና አጫጭር መልዕክቶችንም ማስተላለፍ፣
- አንድ ዋና ጉዳይ በመምረጥ የፓነል ውይይት ማካሄድ፡- ይበልጥ ተጋላጭ እና ትኩረት የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎችን ማዕከል ያደረገ እና የተመረጠ በኤችአይቪ/ኤድስ መከላከል፣ ምርመራ እና የፀረ ኤችአይቪ ህክምና፣ ድጋፍና እንክብካቤ ጉዳዮች በክልል/ከተማ አስተዳደር፣ በዞን/ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ እንዲሁም በሴክተሮች በየደረጃው የፓናል ውይይት ማካሄድ
- ከመሪ ቃሉ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፖስተሮችና ባነሮች ማዘጋጀትና ማሰራጨት
- በዋዜማው ምሽት የሻማ ማብራት ሥነ-ሥረዓት እንዲኖር ማድረግ፣
- እንደየአካባቢው ሁኔታ የሙዚቃ ባንድ፤ የወጣቶች የፀረ-ኤድስ ክበባትን፤ የፖሊስ የማርች ባንድን በመጠቀም በታላላቅ ጎዳናዎችና ህዝብ አዝወትሮ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች እየተንቀሳቀሱ ንውናቄ መፍጠር፡ የተመረጡ አጫጭር መልዕክቶችንም በማይክሮን ማስተላለፍ፣
- ስፖርታዊ ውድድሮች በትምህርት ቤቶችና ወጣቶች በሚሰበሰቡበሰቸው ቦታዎች ማካናወን
- በባህላዊ ትርዒቶች፣ በሥነ-ጽሁፍ፣ ድራማና ፓናል ውይይት ማክበር፣

**II.** በዕለቱ የሚከናወኑ ተግባራት፣

- በጤናው ዘርፍ ባሉ ከፍተኛ አመራሮች ዕለቱንና የወቅቱን መሪ ቃሉን መሰረት በማድረግ  መግለጫ (Press release) እንዲሰጥ ማድረግ።
- የንቅናቄ መድረክ በማዘጋጀት በአመራሮችና በሚመለከታቸው አጋር ድርጅቶች ወቅታዊ መልዕክቶች ተዘጋጅተው እንዲተላለፉ ማድረግ፣
- በየደረጃው ያሉ አመራሮች ለጉዳዩ ትኩረት የሚሰጡበትን ቃላቸውን እንዲያድሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት
- በከፍተኛ አመራሮች የሚመራ የምክክር መድረክ ማዘጋጀትና ውሳኔዎችን ማስተላለፍ፣

**III.** ከበዓሉ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራት **(Post-WAD 2020 Activities)**

- የተላለፉ ውሳኔዎች ዓመቱን ሙሉ ተጠናክረው መተግበራቸውን ለመከታተል የክትትል ዕቅድ ማዘጋጀትና ተፈጻሚነቱንም በየጊዜው መገምገም።
- ንቅናቄውን መሰረት በማድረግ የተጀመሩ ተግባራት ዓመቱን ሙሉ እንዲከናወኑ አቅጣጫ ማስቀመጥ።
- ከዕለቱ በፊት በዕለቱ የተከናወኑ ተግባራትን (መርሃግብሮች) ሪፖርት ማጠናቀር እና በየደረጃው ለሚገኘው የጤናው መዋቅር መላክ።

ስለሆነም የ 2015 ዓም የዓለም ኤድስ ቀን ሲከበር ሁሉን አሳታፊ እና ተደራሽነትን ሊያረጋግጥ በሚችል መልኩ መከናወን ይገባዋል።

በተግዳሮት ደረጃ የተነሱትን ለመቅረፍ ግልፅ መግባባት መደረሱን ማረጋገጥ። የአመራሩን ትኩረት እንደገና ለማሳደግ በየደረጃው ያሉ የጤና አመራች ቁርጠኛ ሆኖ መስራት። ወረርሽኙን ለመቆጣጠር በሚያስችሉ ፕሮግራሞችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ነቅሶ በማውጣት ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ መስራት ያስፈልጋል።

ከዚህም በተጨማሪ፡-

- ✓ በማህበረሰቡ በተለይም በወጣቶች የሚታየውን ቸልተኝነትና መዘናጋት ለመቅረፍ የጭግሩን አሳሳቢነት ተከታታይነት ባለው መንገድ መረጃዎችን (Demand creation) ማስተላለፍ።
- ✓ በኤችአይቪ ቅድመ መከላከል ላይ የሚታዩ የትኩረት ማጣትና የአፈጻጸም ክፍተቶች በማስተካከል መስራት።
- ✓ በአፍላና ወጣቶች እንዲሁም ህጻናት ላይ የሚታየውን የ 3 ቱ 95 ዝቅተኛ አፈጻጸም መገምገምና የተሻለ ውጤት እንዲመጣ መስራት።
- ✓ ኤችአይቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል ስራችን ውጤታማ እንዲሆን የሚመለከታቸውን ሁሉ አስተባብሮ መስራት።
- ✓ ኤችአይቪ በደማቸው ለሚገኝ ወገኖች እና ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናት በድጋፍና እንክብካቤ ሥራዎች ተደራሽን ማረጋገጥ
- ✓ በተቋማት የሚተገበረውን የኤችአይቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ ሥራዎች እንዲጠናከሩ መስራትን ማጠናከር ከበዓሉ በኋላ የነሚከናወኑ ተግባራት ሊሆኑ ይገባል።

*EQUALIZE!!!*

ፍትሀዊና ተደራሽ የኤችአይቪ/ኤድስ አገልግሎት!!

ጤና ሚ/ር